# “ጭንጋፍ (ምቱር) ፓትርያርክ”

**ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ**

nigatuasteraye@gmail.com

**የካቲት ፳፻፭ ዓ.ም.**

*ማሰሰቢያ፦ “ወለእመ ተራድአ በመኳንንተ ዝንቱ ዓለም፡ወተሠይመ ለቤተ ክርስቲያን እምሃቤሆሙ ይትመተር ወይሰደድ ውእቱኒ ወኵሎሙ እለ ተሳተፍዎ”(ፍ.ነ. ፻፸፭) ማለትም፦ “በመንግስት ድጋፍ የተሰየመ ግለ ሰብ ጭንጋፍ ነው”። በቦታው እንዲቀመጥ የተባበሩት ሰዎችም ህይወት የሌለውን ህይወት ያለው በማስመሰል የተባበሩ ናቸውና ጭንጋፎች (ምቱራን) ናቸው።*

*“ይትመተር” ማለት፦ ይጨንገፍ ማለት ነው። “ይሰደድ” ማለት ደግሞ፤ ጭንጋፍ ሆኖ በተወለደ ህይወት አልባ ውራድ ላይ የሚፈጸመው ስርአት ይድረስበት ማለት ነው። ሊወለድ ነው እየተባለ የሚታወጅለት ይህን ግለ ሰብ፤ በመንበሩ ላይ አጽናው ብለን በቅዳሴያችን ልናወሳው ይቅርና፤ “አርህቅ እግዚኦ እምኔየ። ወእምነ ኵሉ ህዝብከ። ወእምዝንቱ መካን ቅዱስ ዘዚአከ”(ሥ.ቅ. ገጽ ፴ ቁ ፴፰) እያልን ከፍ ባለ ድምጻችን ከግላችን፤ ከማህበራችንና ከተቀደሰው መንበራችን እንዲርቅ የምናውጅበት ምቱር ፓትርያርክ ነው። መመሪያችን “ወእለ ሴሙ ላዕሆሙ መገብተ ከሐድያነ ንኮንኖሙ በግዘት በኵሉ መዋዕል”(ፍ.ነ. ፻፩፥ ፳፫) እንዲል ይወገድ የሚለው ምቱሩን (ጭንጋፉን) ብቻ ሳይሆን ሿሚዎችንና የተሰማሙትን ሁሉ ነው።*

# *መግቢያ*

**“እመኒ ሞአ በጉሁሉት ምቱር ውእቱ” (ፍ.አ. ፭. ቁጥ. ፻፸፯)**

**“በሽፍጥ ምርጫ በመንበር ላይ የሚቀመጥ ምቱር” ማለትም ‘ህይወት የሌለው ጭንጋፍ’ ነው። በባህላችን የአዕምሮ መታወክ ካልገጠመን በቀር፤ ውራድ ወይም ጭንጋፍ ሆኖ የተወለደውን ሰውም ሆነ እንስሳ ለማሳደግ ከናቱ ማህጸን ተቀብሎ የሚያቅፍ የለም።**

**ህዝብ ሳይመርጠው፥ እግዚአብሄር ሳይጠራው ወደ ፓትርያርክነት የሚመጣ እንደ ውርጃ ይቆጠራል። እንዳይከሰት ጥንቃቄ ይደረግ ዘንድ መጽሐፋችን መመሪያ ይሰጣል። በዘመናችንም የውስጥና የውጭ ሲኖዶሶች በሰየሙት ዛሬ የሞት ስቅላት አቶ ስብሀት ነጋ በፈረዱበት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰላምና አንድነት ጉባኤ (የሰላሙ ቡድን) አማካይነት ተጨንግፎ ከሚወለድ ፓትርያርክ እንድናለን ብለን ተስፋ አድርገን ነበር።**

ነገር ግን የወያኔ መንግስት ይህን ሁሉ ጥያቄ ሳይቀበል፤ የህዝቡንም ፈቃድ ጥሶ በመለመላቸው ጳጳሳት አዋላጅነት ጭንጋፍ (ምቱር) ፓትርያርክ ለመውለድ በምጥ ላይ መሆኑን በብዙኀን መገናኛዎች ሰማነው። የህዝበ ክርስቲያኑና የሊቃውንቱ ክህነታዊ ተማህጽኖ የመነጨበት የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ እንደሚጠቁመን፤ አሁን በሚከናወነው መንገድ ጨንግፎ የሚወለደውን ፓትርያርክ "ሕልፈቱ ቅድመ አስተርእዮቱ" ብላ ቤተ ክርስቲያናችን ትጸየፈዋለች። ይህን ለመግለጽ የሞከርኩባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው።

- ፩ኛ፦ተጨንግፎ የሚወለደው ፓትርያርክ
- ፪ኛ፦እንዴት ጨነገፈ
- ፫ኛ፦መቀበል የለብንም
- ፬ኛ፦እግዚአብሔር የከፈተው በር
- ፭ኛ፦የእርቀ ሰላሙ ቡድን ሃላፊነት
- ፮ኛ፦ የህዝበ ክርስቲያኑ ሐላፊነት

ከዚህ በመቀጠል "ተጨንግፎ የሚወለደው ፓትርያርክ" በማለት የቀረጽኩትን የመጀመሪያውን አንቀጽ በማብራራት ይህችን ጦማር እጀምራለሁ።

# ፩ኛ፦ ጨንግፎ የሚወለደው ፓትርያርክ

የካቲት ፳፩ ስለሚወለደው ፓትርያርክ ስናስብ ከአቡነ ጳውሎስ የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን። አቡነ ጳውሎስን ይህ መንግስት ከሜዳ አግኝቶ በማደጎ አሳደጋቸው እንጅ ጸንሶ የወለዳቸው አይመስሉም። ይህን ለማለት ያስገደደኝ፤ እርቁ እንዲጀመር በፈቀዱት በአቡነ ጳውሎስ ላይ አቶ ስብሀት ነጋ "እርቁ እንዲጀመር በመስማማታቸው ተሳስተዋል" ብለው በወረወሩባቸው ትችት እራሱ የወያኔ መንግስት አቡነ ጳውሎስን የጉዲፈቻ ልጅ አድርጓቸዋል። የኢ.ህ.ዴ.ግ. ልጅ መስለው የተገኙት በቦታው ከተሰየሙ በኋላ ነውና ማደጎ ነበሩ ማለት ነው። ይህ ዛሬ ሊወለድ ነው ተብሎ የተነገረን ፓትርያርክ ከአቡነ ጳውሎስ ለየት ያለ ኢ.ህ.ዴ.ግ.ን በጫካ በነበረበት ጊዜ በአካሉ በሥጋውና በነፍሱ አስመሎ ይወልደው ዘንድ የጸነሰ ነው። ያጸናነሱን ሁኔታ የቀድሞው የሕ.ወ.ሓ.ት. ሊቀመንበር ከነበሩት ከዶክተር አረጋዊ በርሄ መጽሐፍ እንመልከተው። (ዝርዝሩን እዚህ ላይ በመጫን ያንብቡ)።

## *የዶክተር አረጋዊ ታሪካዊ ሕሀያው የምስክርነት ቃል፦*

*"የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር በ1979 አመተ ምህረት አስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርሀ ግብር ለሚመለምላቸው ቀሳውስት ዘረጋ። የማሰልጠኑ ዓላማ ቤተ ክርስቲያኗን ከህዝብ ለይቶ በመምታት ስፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዞት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው።*

*የወረዳ ስልጠና የተጀመረው በጠንካራ ትግሉ የታወቀው ካዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በነገረ መለኮት ትምህርት የተመረቀው ገብረ ኪዳን ደስታ ነው። የስልጠናውም ይዘት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጠቅላላ መዋቅራዊ አስተዳደር በትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት ባለሟሎች መተካትና በቤተ ክርስቲያኒቱ አካባቢ የትግርኛ ቋንቋ እንዲሰፍን ማድረግ ነው። በዚህ መንፈስ ተቀረጸ የተዘረጋው እቅድ በየሰበካውና አጥቢያው ያሉትን ቄሶችና ምእመናኑን ቤተ ክርስቲያኒቱ ጠብቃ ካቆየችው ታሪክና ብሄራዊ መዋቅር እየገነጠሉ በማስኮብለል ወደ ነጻ አውጭው እምባ መሰብሰብ ነው። መነኮሳት በመምሰል ደብረ ዳሞ ወደ መሳሰሉት ገዳማት ሰርጎ በመግባት የድርጅቱን እቅድ በማስተጋባት የሚያዳክም አጥኝ ኃይል በስብሀት ነጋ መሪነት ተመሰረተ። የማሰልጠኑ ተግባር ከተፈጸመ በኋላ፤ የሰለጠኑት አስመሳይ መነኮሳት በትግራይ ምድር ዙሪያ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ከዋናው ጽፈት ቤት መገንጠልን በ1987 እና በ1989 ተግባራዊ እንዲያደርጉት አደረገ። ከነጻ አውጭው አመራር የሚቀበለው መነኮሳት እየመሰለ ሰርጎ የገባው አስመሳይ ቡድን፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና መዋቅር ተገንጥሎ ከነጻ አውጭው ጋራ ጎን ለጎን የማካሄ ስራውን ቢሮ ከፍቶ ጀመረ። በዚህ ጊዜ ከዋናው ጽ ቤትና ከነጻ አውጭው ትእዛዝ በሚቀበሉት ቡድኖች መካከል የጎላ ልዩነት በግልጽ መታየት ጀመረ። እስከ 1990 ድረስ ሁለቱም ጎን ለጎን ሲሰሩ ከቆዩ በኋላ፤ ነጻ አውጭው መቀሌን ሲቆጣጠር፣ ከዋናው ጽ ቤት አመራር ይቀበል የነበረው መቀሌን ለቆ በ1991 ወደ ደሴ ሲሄድ፣ በነጻ አውጭው ሰር ይመራ የነበረው ቡድን መቀሌውን ተቆጣጠረ"*

## ከዶክተር አረጋዊ በርሄ መጽሐፍ ከጠቀስኩት አንቀጽ ፬ ቁልፍ ሀረጎች እነሆ!

- ፩ኛ፦ "መነኮሳት በመምሰል ደብረ ዳሞ ወደ መሳሰሉት ገዳማት ሰርጎ በመግባት የድርጅቱን እቅድ በማስተጋባት ቤተ ክርስቲያኒቱን የሚያዳክም አጥኝ ኃይል በስብሀት ነጋ መሪነት ተመሰረተ"
- ፪ኛ፦ "ከነጻ አውጭው አመራር የሚቀበለው መነኮሳት እየመሰለ ሰርጎ የገባው አስመሳይ ቡድን፣ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና መዋቅር ተገንጥሎ ከነጻ አውጭው ጋራ ጎን ለጎን የማካሄድ ስራውን ቢሮ ከፍቶ ጀመረ"
- ፫ኛ፦"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ጠቅላላ መዋቅራዊ አስተዳደር በትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት ባለሟሎች መተካትና በቤተ ክርስቲያኒቱ አካባቢ የትግርኛ ቋንቋ እንዲሰፍን ማድረግ ነው"
- ፬ኛ፦ "ነጻ አውጭው መቀሌን ሲቆጣጠር፣ ከዋናው ጽ ቤት አመራር ይቀበል የነበረው መቀሌን ለቆ በ1991 ወደ ደሴ ሲሄድ፣ በነጻ አውጭው ሰር ይመራ የነበረው ቡድን መቀሌውን ተቆጣጠረ"በማለት ጸንሳ፤ ወልዳና አሳድጋ የሰጠችን መንደር ትባረክና ብትንትን አድርገው ዶክተር አረጋዊ በርሄ ነግረውናል።

ይህን ይቅርታ የሌለው ደባ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ቀደም ብለው የፈጸሙ አቶ ስብሀት ነጋ ጨካ በነበሩት ጊዜ ካቀዱት የጥፋት ሴራቸው ጋር ስለተጋጨ፤ የጉዲፈቻ ልጃቸውን ሟቹን አቡነ ጳውሎስን እርቀ-ሰላም እንዲጀመር በመፍቀዳቸው ኮንነዋቸዋል። "ዕርቅ ለመፈጸም በማለት ሰዎችን ሲልኩ የነበሩ ቄሶች መሰቀል አለባቸው" ቢሉ፤ "እምውስተ ርኩስ ምንትኒ ኢይወጽእ ንጹህ ወበውስተ ሀሰት በአይቴ ይትረከብ ጽድቅ" (ሲራ ፴፬፥፬) ማለትም፦ "ከአህያ መስዋዕት የሚሆን በግ እንደማይወለድ፤ ከሐሰተኛ ሕልምኛም እውነተኛ ነገር አይገኝም" ብሎ ጠቢቡ የተናገረውን ስለምናውቅ ዛሬ አቶ ስብሀት ነጋ ይሰቀሉ እያሉ አረመኔያዊ ንግግር ቢናገሩ ሊያስደንቀን አይገባም። ባለፈው ስህተታቸው ንስሀ መግባት ሲገባቸው፤ ጭንጋፍ (ምቱር) ፓትርያርክ ለማሸከም ባላቸው ድፍረትና ንቀት በመቀጠላቸው እጅግ ልናዝንላቸው ይገባል። ከኛ የሚጠበቅብን ሊያሳዝሉን የሚሞክሩትን ጭንጋፋቸውን (ምቱርን) ፓትርያርክ እራሳቸው አዝለው እንዲዞሩ ማድረግ ነው። ይልቁንስ በመምጣት ላይ ያለውን የነ አቶ ስብሀት ነጋን ፓትርያርክ ምን እንዳስጨነገፈው? ቤተ ክርስቲያናችን የምትነግሪን "ምን አለሽ?" ብለን እንጠይቃት።

# ፪ኛ፦ምን አስጨነገፈው?

ቤተ ክርስቲያናችን “ይኩን በስምረተ ሕዝብ ዘይሰየም ላዕሌሆሙ። በህርየተ ኩሎሙ ህዝብ”(ፍ. አ. .፲) አማኞቹ በሰላም በስምምነት መርጠውት እሱም በምልአ ልብና በትፍስህት መምራት የሚችል ሲሆን ብቻ ነው ህይወት ያለው ፓትርያርክ ብለን የምንቀበለው። ይህ ሊወለድ ነው ተብሎ የተነገረን ግን በህዝበ ክርስቲያን ሳይፈለግ በካህናት ሳይደገፍ ይልቁንም መራር ተቃውሞ እየሰማ በግርግር በሸር በመንግስት ድጋፍ የሚሰየመውን ፓትርያርክ ቤተ ክርስቲያናችን ጭንጋፍ “ምቱር” ትለዋለች። ሰዎች ሲቃወሙ የተቃውሞ ድምጻቸው እውነትነት እንዳለውና በሀሰት እንደሆነ ተመርምሮ እስኪደረስበት ድረስ፤ ጥቂቶችም ቢሆኑ የተቃውሞ ድምጻቸው ተከብሮ የተጀመረው የምርጫ ሂደት መቆም አለበት።

ተቃውሞው ተመርምሮ እስከ ሶስት ከደረሰ ማለትም የሚቃወመው የህብረተ ሰቡ አካል ሲሶው ከሆነ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምና መረጋጋት ሲባል የታጨው ግለሰብ ገለል በማለት የሲሶው እጅ ህብረተ ሰብ ድምጽ መጽናትና መከበር አለበት።

## የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት መርሆ እንመልከት፦

- ፩ኛ፦ “ወኢይከውን አሐዱ ሰማእት ከመ ይኩን ስምዐ ላዕለ ኩሉ ጌጋይ ወበኩሉ አበሳ ዘአበሰ በአፈ ክሌቱ ወሠለስቱ ሰማዕት የህልቅ ኩሉ ነገር”(ዘዳግም ፲፱፡፲፭)። በደለኛ ተብሎ የሚወቀስና የሚከሰስ ሰው ክሱ ባንድ ምስክር ብቻ አይረጋገጥ። ክሱ ወቀሳው በሁለት በሶስት የምስክር ድምጽ ይጽና።
- ፪ኛ፦ “ወእመሰ ኢሰምአከ ንሣዕ ምስሌከ በዳግም አሐደ አው ክልዔ ከመ በአፈ ክልኤ ወሠለስቱ ሰማእት ይቀውም ኩሉ ቃል” ማቴ ፲፰፡ ፲፮። ምከረው ካልሰማህ በሁለት ምስክር ነገር ይጸናልና በሁለት በሶስስት ምስክር ይዘህ ምከረው።ከዚያ በኋላ እንደ አረመኔ ቁጠረው።
- ፫ኛ፦ “አኮኑ በአፈ ክልዔቱ ወሠለስቱ ሰማእት ይቀውም ኩሉ ነገር”(፪ቆር ፲፫፡፩) በሁለት በሶስት የምስክር ድምጽ ሁሉ ነገር የሚጸና አይደለምን?

በኦሪት፥ በክርስቶስና በሐዋርያት ተደጋግሞ የተነገረ ይህ ትዕዛዝ በሀሰት ወይም በአድማ ጻድቁን ወይም ተገቢውን ሰው ለአገልግሎት ሲሰየም በምቀኝነት በተንኮል እንዳይበላሽ የተደረገ ጥንቃቄ ነው። “ይኩን በስምረተ ሕዝብ ዘይሰየም ላዕሌሆሙ። በህርየተ ኩሎሙ ህዝብ”(ፍ.አ.፲) የሚለው ትእዛዝ በመመሪያችን የተመዘገበው ከኦሪት ከክርስቶስና ከሐዋርያት ትእዛዝ መንጭቶ ነው።

አሁን ሊሰየም በታቀደው ፓትርያርክ ምርጫ ላይ እየጎረፈ ያለው የተቃውሞ ድምጽ ብዛት፥ እንድንለካባቸው ከላይ ከተገለጹት መስፈርቶች በላይ ነው። ይህን ተቃውሞ ሰብሮ የሚመጣውን መሳይ ፓትርያርክ መመሪያችን ምቱር (ጭንጋፍ) ይለዋል። ከዚህ በታች ከ፩ እስከ ፯ ተራ ቁጥር ምቱር ያደረጉትን (ያስጨነገፉትን) ማስረጃዎች በጥንቃቄ እንመልከታቸው፦

- ፩ኛ፦ በሞት ከተለዩን ሊቃውንቱ መካከል አንዱ በህይወት ያሉት ሊቀ ካህናት መራዊ ተበጀ “የቁጥር ዶክትሪን የለንም” ብለው በመጀመሪያ ተቃውሟቸው ከእነ አቶ ስብሀት በመወለድ ላይ ያለውን ምቱርነት በመግለጽ አስጨንገፈውታል።
- ፪ኛ፦ በአቃቤ መንበረ ፓትርያርኩ የሚመራው የውስጡ ሲኖዶስ ለጤነኛ ፓትርያርክ አሰያየም ይመች ዘንድ ስምምነት እርቅና ሰላም እንዲቀድም አምኖበት ለእርቁ ድርድር አቡነ አትናቴዎስን፥ አቡነ ገሪማንና አቡነ ቀውስጠስን ወክሎ መላኩ ጭንጋፍ (ምቱር) አድርጎታል።

- ፫ኛ፦ በሁሉም ወገን ታምኖበት በነ ሊቀ ማእምራን አማረ የተመሰረተው አስታራቂ ቡድን መመስረቱና፤ ይህ ሳይቋጭ ለፓትርያርክ ምርጫ የተደረገውን ሩጫ የቡድኑ ተቃዉሞ አስጨንግፎታል።
- ፬ኛ፦ምርጫ ከምታሰቡ በፊት እርቀ ሰላሙ እንዲፈጸም የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት መቶ አለቃ ግርማ ወልደጊዮርጊስ ያቀረቡት ጥሪም አስጨንግፎታል። ([ዝርዝሩን እዚህ ላይ በመጫን ያንብቡ](#))
- ፭ኛ፦ በአገር ውስጥና በውጭ ያለው የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ሁሉ ከምርጫው በፊት እርቁ እንዲቀድም ያቀረቡት ጥያቄ አስጨንግፎታል።
- ፮ኛ፦የላካቸውን ሲኖዶስ እና የታላከውን ቡድን ወክለው አቡነ አትናቴዎስ በአሜሪካ ራዲዮ “የጀመርነው እርቅና ሰላሙ ከዳር ሳይደርስ ለፓትርያርክ ምርጫ የሚደረገውን ዝግጅት እንቃወማለን” በማለት ያሰሙት የተቃውሞ ጥሪ፤ ከዚህ በላይ የተደረደሩትን ፭ የምስክርነት ድምጽ ማሳረጊያና መደምደሚያ ሆኖ አስጨንግፈውታል ወይም (ምቱር)አድርጎታል።

<u>ልንይዛቸውና ልንመራባቸው የሚገቡን ከዚህ በላይ ይተገለጹትን እንጅ ወደ ኢምባሲው ሄደው ለነአቶ ስብሀት ነጋ ፖለቲካ ጥቅም ታስቦ recalculated ተደርገው ከዚህ በታች የቀረቡትን አይደለም፦ ከዚህ በታች ከ፩ እስከ ፬ የተዘረዘሩት ምክንያቶችም ቢሆኑ እነ አቶ ስብሀት ነጋ ሊወልዱት በምጥ ያለውን ፓትርያርክ የበለጠ አስጨንግፈውታል ወይም (ምቱር)</u>አድርጎታል።

## <u>ዋና ዋና ነጥቦችን እንመልከታቸው፦</u>

- ፩ኛ፦ የአገሪቱ ፕሬዝደንት በግል ክርስትናቸውም ሆነ ፕሬዝደንታችው ቤተ ክርስቲያኒቱ ያቀፈችው ከ፵፩ ሚሊዮን ባለይ ነው የሚባለው ህዝብ የፈቀደውን ለማንጸባረቅ ባለባቸው ግዴታ፤ ከፓትርያርክ ምርጫ በፊት ስምምነቱ እንዲፈጸም የሰጡትን የተቀደሰ ሀሳብ እንዲቀይሩ “የኢሀደግ ፈቃድ አይደለም” በማለት ከአቃቤ መንበረ ፓትርያርኩ ከአቡነ ናትናኤል የተሰነዘረባቸው ተግሳጽ ሽፍጥ በመሆኑ አስጨንግፎታል።
- ፪ኛ፦በቅርስነት ከምንመለከታቸው አባቶቻችን ከአቡነ አትናቴወስ ቃል ያፈነገጠ ወረቀት የሰላም ቡድኑ ከውጩ ሲኖዶስ ጋራ ወግኗል የሚል ቃል ንቡረ እድ ኤልያስ የተባሉት ሰው በአዛውንቶቹ አባቶች ስም ጽፈው ያሰራጩት ሽፍጥ አስጨንግፎታል።
- ፫ኛ፦ ከዚያም “ዕርቅ ለመፈጸም በማለት ሰዎችን ሲልኩ የነበሩ ቄሴች መስቀል አለባቸው” በማለት አቶ ስብሀት ነጋ የተናገሩት አረመኔዊ የስቅላት ፍርድ አስጨንግፎታል።

በነዚህ ሁሉ ውስብስቦች (complication) የሚወለደው ፓትርያርክ በገዛ እትብቱ ታንቆ በመጨንገፍ እንዲወለድ አድርጎታል። ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ነገሮች ተጨንግፎ የመጣውን ፓትርያርክ ቤተ ክርስቲያናችን እንዳንቀበለው ታዝዘናለችና <u>መቀበል አይኖርብንም</u>። ይህንም በጥንቃቄ አብረን እንመልከተው።

# ፫ኛ፦<u>መቀበል አይኖርብንም</u>።

ከዚህ በላይ በተገለጸው ትርምስና ግርግር ተመርጫለሁ ብሎ የሚመጣውን ፓትርያርክ ከ፩ እስከ ፮ ተራ ቁጥር ከዚህ በታች ተብራርተው የተገለጹት የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ እንዳንቀበለው በአጽንኦ ያስገነዝበናል።

**፩ኛ፦ ቅዱስ ጴጥሮስ** "ረዐዩዘሁሎ ኅቤክሙ መርዔቶ ለእግዚአብሄር እንዘ ተአቅብዎሙ ወኢ.ትቅንይዎሙ በኩርሀ አላ በጽድቅ በእንተ እግዚአብሐር እንዘ ኢትሬብሀዎሙ አላ በምልአ ልብክሙ ወበትፍስሀት፡ እንዘ ኢትትሄየሉ ሕዝቦ ለእግዚአብሄር አላ አርአያ ኩንዎሙ ለመርዔቱ" (፩ኛ ጴጥ ፭፡፪) ይህም ማለት፦ የእግዚአብሄርን ህዝብ በጥንቃቄ ምሩ። ምእመናን ሳይፈቅዱ በተጽእኖ አስገድዳችሁ ለመምራት አትሞክሩ" የሚለው ጥብቅ ትእዛዝ ነው። ሊቃውንት አበው፤ በአስረጅና በዓቢይ አገባብ እየታጀቡ ከሁለት ጊዜ በላይ ተደጋግመው የሚቀርቡ ትእዛዞች ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባ ጥብቅ ትእዛዛት ናቸው ብለው አስተምረውናል። ከተቃወሱ ለጥገና የሚያስቸግር ሀውክ ይፈጠራል ይላሉ። እንዳሉትም በዚህ አረፍተ ነገር ለአጽንኦተ ትእዛዝ ተደጋግመው የተገለጹት በዓቢይ አገባብ አጎላማሽነት የቀረቡት፤ የካቲት ፳፩ ቀን በሚሰየመው የፓትርያርክ ሹመት ተጥሰዋል።

ሀ፦ አላ ረዐዩ............ በጽድቅ

ለ፦ አላ ረዐዩ............በምልአ ልብክሙ ወበትፍስሀት፡

ሐ፦ አላ ኩንዎሙ አርአያ............ተብለው የተገለጹት ዓበይት ነገሮች በነ አቡነ እስጢፋኖስ አዋጅ ተጥሰዋል። በነ አቶ ስብሀት ነጋ ተመልምሎ የሚመጣው ፓትርያርክ በሐዲስ ኪዳን ትእዛዝ ላይ ተመስርተው በመመያችን ላይ ተገልጸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ትእዛዞች የጣሳቸውን እንመልከት።

**፪ኛ፦** "ወይትነስኡ ላዕሌሁ በጽድቅ ወኢይህድግዎ ይትዐደው ሃበ አባግዐ ክርስቶስ"(ፍ.አ ፭ ቁ. ፻፹፭-፺) በሚለው አንቀጽ ከሌሎች አፍራሽ ትእዛዞች ጋራ ኢይኅድግዎ የሚለው ጥብቅ ትእዛዝ ሶስት ጊዜ ለአጽንኦተ ነገር ተደጋገመ።

ሀ፦ ኢይኅድግዎ፦ይትዐደው፤ መመሪያውን ጥሶ የሚመጣውን ምእመናን ችላ አይበሉት።

ለ፦ ኢይኅድግዎ፦ይንበር፤ በመንበሩ እንዲቀመጥ ምእመናን እድል አይስጡት

ሐ፦ ኢይኅድግዎ፦ ይትመየጥ፤ ካባረሩትም እንኳ በኋላ እንዳይመለስ ምእመናን በሩቅ ይጠብቁት" ተብሎ በመደጋገም ተነገረ።

**፫ኛ፦** "ለእመ ይትጋአዙ ሰብአ ሀገር አው አህጉር እስከ ይትከፈሉ ሃበ ፪ቱ ክፍል ወበዛቲ ምክንያት ተሠይመ ካልዕ ኤጲስ ቆጶስ ለይሕትቱ ጥዩቀ በእንተ ዝንቱ። ወለእመኒ ኢረከቡ ለዕለ ቀዳማዊ ኤጲስ ቆጶስ ዘይደሉ ለመቲሮቱ ለይንበር በመካኑ። ወእመሰ ረከቡ በላዕሌሁ ለይሲሙ በመካነ ዚአሁ ዘአልቦ ነውር ውስቴቱ ወለዝንቱ ያውግዝዎ"( ፭፡ ፻፸) አከራካሪ ነገር ተፈጥሮ ሰው ተከፋፍሎ ሳለ፤ የተነሳው ነገር መስመር ሳይዝ በግርግር ፓትርያርክ ቢሰየም ጉዳዩን በጥንቃቄ ይመርምሩት። በመጀመሪያው ሰው ላይ ምንም የእምነት ሕጸጽ ከሌበት ይመለስ። የሚለው ትእዛዝ ሳይቋጭ ቁጥሩ ከሶስት እጅ በላይ የሆነው ህዝብ እየተቃወመው የመጣውን ፓትርያርክ መቀበል የለብንም። "ወለእመኒ ኢረከቡ" እና "ወእመሰ ረከቡ" በሚሉ አበይት አገባቦች ታጅባ የቀረበችው "ረከቡ" የተባለችው ግስ በነ አቶ ስብሀት ነጋ የስቅላት ፍርድ ማስፈራሪያ የምትታለፍ አይደለችም።

**፬ኛ፦**"ወለእመ ተራድአ በመኳንንተ ዝንቱ ዓለም፡ወተሠይመ ለቤተ ክርስቲያን እምሃቤሆሙ ይትመተር ወይሰደድ ውእቱኒ ወኩሎሙ እለ ተሳተፍዎ"(፻፸፭) ማለትም፦ በመንግስት ድጋፍ የተሰየመ ግለ ሰብ ጭንጋፍ ነው። በቦታው እንዲቀመጥ የተባበሩት ሰዎችም ህይወት የሌለውን ህይወት ያለው በማስመሰል የተባበሩ ናቸውና ጭንጋፎች (ምቱራን) ናቸው። "ይትመተር" ማለት፦ ይጨንገፍ ማለት ነው። "ይሰደድ" ማለት ደግሞ፤ ጭንጋፍ ሆኖ በተወለደ ህይወት አልባ ውራድ ላይ የሚፈጸመው ስርአት ይድረስበት ማለት ነው።

**፭ኛ፦** "ዘተማኅጸነበእንተ ምግብናሁ ለሰብአ አፍአ አው በመኳንንተ ዓለም ይርድእዎ በእንተ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዘ የሀስስ በዝንቱ አኅስሮቶሙ ለሕዝበ እግዚአብሄር"(፻፸፺) በመንግስት ርዳታና አጋዥነት የገባ ፓትርያርክ ህዝበ እግዚአብሄርን ያወረደ ተጨንግፎ የመጣ ነው። ጭንጋፍ ሆኖ በተወለደ ህይወት አልባ ውራድ ላይ የሚፈጸመው ስርአት ይድረስበት ማለት ነው።

፯ኛ፦ “ይትመተር ዘይነስእ ሢመተ ክህነት በኅልያን፤ አው በተገርሞ፤ አው በአድለዎ ፤ አው በትምይንት፤ አው በአሰፈዎ ሕልያን (ፍ. አ ፯፡ ቁ፡ ፪፻፷፬)” ጥብቅ ትእዛዝ ያዘለችውን ይህችን ሐረግ እንተነትናት። የዚህች ሐረግ ማሰሪያ ግስ “ይትመተር” ናት። ማለትም ይጨንገፍ ማለት ሲሆን፡ የሚያስጨነግፋትም ምክንያቶች ከዚህ በታች የተደረደሩት ናቸው።

በህልያን............................በፍቅረ ሲመት የተበከለ ሕሊና

አው በተገርሞ......................በምድራዊ ሥልጣን አስፈራሪነት የመጣ ፓትርያርክ

አው በአድለዎ......................ሚዛኑን ሳያሟላ የመጣ

አው በትምይንት....................በማን አለብኝ ስሜት የመጣ ፓትርያርክ

አው በአሰፈዎ ሕልያን..............በመሞዳሞድ የመጣ ፓትርያርክ

ይህች ሀረግ ብቻ በየተሸከመችው የቤተ ክርስቲያናችን ትእዛዝ: እነ አቶ ስብሀት ነጋ የሚሰይሙትን ፓትርያርክ ተቀብለን ቅዱስ ብጹዕ ብለን በቅዳሴያችን ልናስታውሰው አይገባም።

“ወንህነኒ ሰበክነ ስመከ ልዕልተ ወክብርተ ውስተ ኩሎን አብያተ ክርስቲያናት ወውስተ ኩሎን አህጉር ወበህውርት ወአዘዝነ ይዝክሩከ በኩሉ ቅዳሴያት”(ሃ.አ. ፻፬፡፲፫) ከሚለው ከኦርቶቶክሳዊው መርሆችን ጋራ ያጋጨናል። በዚህ አረፍተ ነገርበቅዳሴያችን ስሙን እንድናስታውሰው የታዘዝነው ቃሉን ሳይለዋወጥ፥ ሸቀጣ ሸቀጥ ሳይደባልቅ፥ ለነገረ መለኮቱ፥ ለሞራሉ፥ ለተየሰየመለት ዓላማ ጸንቶ ለቆመ፥ በእውቀቱ፥ በችሎታው፥ በታማኝነቱ ታምኖበት ያለአንዳች ተቃውሞ ለተመረጠ አባት ብቻ ነው።

ሊወለድ ነው እየተባለ የሚታወጅለት ይህን ግለ ሰብ ግን፤ በመንበሩ ላይ አጽናው ብለን በቅዳሴያችን ልናወሳው ይቅርና፤ “እርህቅ እግዚኦ እምኔየ። ወእምነ ኩሉ ህዝብከ። ወእምዝንቱ መካን ቅዱስ ዘዚአከ”(ሥ.ቀ. ገጽ ፴ ቁ ፴፷) እያልን ከፍ ባለ ድምጻችን ከግላችን፤ ካንድነታችንና ከተቀደሰው መንበራችን እንዲርቅ የምናውጅበት ምቱር ፓትርያርክ ነው።

ከኛ እንዲርቅ ይህን የምናውጀው ምቱር ሆኖ በመጣብን ፓትርያርክ ብቻም አይደለም። “ወእለ ሴሙ ላዕሆሙ መገብተ ከሐድያነ ንኬንኖሙ በግዘት በኩሉ መዋዕል”( ፻፩፡ ፳፫) ይህን ምቱር ፓትርያርክ በላያችን ላይ የጫኑብን እና በሀሳቡም የተስማሙት ሁሉ ምቱራን ጭምር ከኛ እንዲርቁልን ነው።

አያችሁ! ቅዳሴያችንን ብንመለከተው እኮ “ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ” እያሉ ለሚቀደሱት ለጸወርተ መንበሩ ሱራፌልና ኪሩቤ ቅዳሴ ተሰጥኦ ነው። ይህን ቅዳሴ በመቀደሰ ተሰጥኦውን የምትመልሰዋ ቤተ ክርስቲያናችን “አናቅጽ ሲኦል ኢይሄይልዋ” የተባለችው ናት። ቅዳሴያችን እንደነ ስብሀት ነጋ የመሳሰሉ ነፍሰ ገዳዮች ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ሾልከው የሚገቡበትን ጓዳ እየዘጋ፤ ክርስቶስ የከፈተውን በር እንድንመለከት የሚመራን ነው።

ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን የሰጠችንን ከኦሪቱ ጀምሮ በየእለት ስከምንጠቀምበት መጽሀፈ ቅዳሴያችን ላይ ያለውን ሊቃውንት አበው ያስተማሩንን ሳንለቅ ያተረጓጎማቸውን ስልት ሳንቀይርና ሳንደበላልቅ ቀጥ ብለን ብንሄድ በጓዳ በር ሾልኮ የሚገባውን እያስወጣን በበሩ የሚመጣውን ይደልዎ ብለን በመቀበል ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ከነ ስብሀት ነጋ ወጥመድ ማትረፍ ይቻላል። (የነ ፋሌቅ ወጥመድ የሚለውን ጦማር እዚህ ላይ በመጫን ያንብቡ)።

# ፬ኛ፡የተከፈተው በር

በቅዱስ መጽሐፍ ላይ የተመሰረተው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚነግረን፤ ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የተመሰረተችው ከተለያዩ ቦታወች ባህልና ቋንቋ ለተለመደው ዓመታዊ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም በተጓዘ ሰው።

ታሪኩ እንደሚነግረን፤ ከተለያዩ ቦታዎች በዓለ ጰራቅሊጦስን ለማክበር ኢየሩሳሌም ላይ የተሰበሰቡት ሰዎች ክርስትናን በራሳቸው ቋንቋ ሰምተው ቤተ ክርስቲያንን አዝለው ወደየ አገራቸው ለመመለስ አስበው አልነበረም። ሐዋርያትም ቢሆኑ ባንድ ቤት ተሰብስበው ዘግተው የነበሩት እንዳትበታተኑ ቆዩ የተባሉበትን ምሥጢር በሚገባ ተርደተውና ከተለያየ አካባቢ ለመጣው ሰው በየራሱ ቋንቋ ነግረን እንልካለን ብለው አስበው አልነበረም። ሆኖም እግዚአብሔር በመለኮታዊ እቅዱ ከተለያዩ ቦታዎች ሰዎችን ወደ ኢየሩሳሌም ሰበሰበ። ሐዋርያትንም ባልተረዱት መንገድ ኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አደረገ። ሐዋርያት ዘግተው በተሰበሰቡበት ቤት ላይ ሰውን ሁሉ አንድ አርጎ የሚስብ እሳት መሳይ ኃይል አነደደ። ከሩቅ ቦታ የተሰበሰበው ህዝብ ሁሉ ይገናኝበት ዘንድ በፍርሀት የተዘጋውን ቤት ወደ አደባባይነት ለወጠው።

እንደዚሁ ሁሉ በዘመናችን እግዚአብሔር ተመሳሳይ ስራ በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እየሰራ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን በእርስ በርስ ጥላቻ ዝግ ነበረች። የውስጡም ሆነ የውጭ ሲኖዶስ ተስማምተው ችግሩን ሊፈቱት በሩን ሊከፍቱት ባለመቻላቸው ይልቁንም "ወእመሰ በበይናቲክሙ ትትባልኡ ወትትናሰኩ ተኀልቆ ተርፈክሙ" (ገላ ፭፥፲፭) ከተባለው ደረጃ በመድረሳቸው፤ እነሱ ባላወቁት መንገድ በሰላሙ ቡድን መከሰት ላይ እግዚአብሔር እንዲሰማሙ አደረጋቸው። በሰየሙት ቡድን አጋዥነት እንኳ ችግሩን መፍታት አልቻሉም። እንግዲህ ቢገባንና ብንረዳው እንድንጠቀምበት እግዚአብሄር በሰላሙ ቡድን በኩል ቤተ ክርስቲያናችንን ከነ አቶ ስብሀት ነጋ እንድናተርፋት በሩን አዘጋጅቷል። የሰላሙ ቡድን ይህን ረቂቅ ጥሪ ተረድቶና ተገንዝቦ ከእርቁ በፊት የፓትርያርክ ምርጫ እንዳይታሰብ ድምጽ ያሰሙትን ሁሉ ድርጅቶችን ታላላቅ ሊቃውንት ካህናትንና የተበታተነውን ህዝበ ክርስቲያን በማስተባበር ሃላፊነቱን ይወጣ ዘንድ ታሪካዊ ግዴታ ወድቆበታል።

# ፭ኛ፡ በሰላሙ ቡድን ላይ የወደቀው ታሪካዊ ግዴታ፡

የሰላሙ ቡድን "ዘይፈቅድ ይህንጽ ማኀፈደ ፡አኮኑ ይቀድም ይንበር ወየሀስብ ጻእጻአ እመ ዘየአክሎ ከመ ይሳርር መሰረቶ፡ እመ ስእነ ፈጽሞቶ ኵሎሙ እለ ርእዩዎ ይእህዙ ወይሳለቁላእሌሁ (ሉቃስ ፲፬፡ ፳፰_፴)" የሚለውን የክርስቶስን ቃል መመሪያ አድርጎ ከሆነ: ከላይ ከ፩ እስከ ፬ የተዘረዘሩትን የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያዎች ከመፈጸም አያፈገፍግም። ወደዚህ ተልእኮ ስትገቡም ይህን ግዴታ በመዘንጋት አይመስለኝም። ተልእኮው በቀላሉ ከፍጻሜ እንደማይደርስና መስዋዕትነት እንደሚጠይቅ ሳትረዱ ጀምራችሁት ከሆነ፤ አካባቢያችሁን የመቃኘት አቅም የሌላችሁና ቤተ ክርስቲያናችን ያለችበትን ማእበል ሳትረዱ ዘላችሁ የገባችሁ፤ ወይም በሁለት ልብ ሆናችሁ ጀምራችሁታል ማለት ነው። "ሁለት ሀሳብ ላለው በመንገዱም የሚወላውል ሁሉ ከአምላክ ምንም የሚያገኘው ረድኤት የለም" (ያዕ ፩፥፰) የሚለውን ረስታችሁታል። ወይም በቀላሉ ቢሳካ የባለውለታነትን ውዳሴና የሚገኘውን ጥቅማ ጥቅም ለመሳተፍ፤ ሳይሳካ ቢቀር በቀውስ ላይ ላለችው ቤተ ክርስቲያን ግድ ሳይኖራቻሁ፡ ለራሳችሁ ሰላማዊ ኑሮ ቅድሚያ

በመስጠት ከአጥፊው ቡድን ጋር ያላችሁን ወዳጅነት ቀጥላችሁ ከዚያም ከዚህም በሹመት በሽልማት ለመኖር የምትፈልጉ ያስመስልባችኋል።

ይህ ደግሞ ስለ ቤተ ክርስቲያን አንድነት የሚጨነቀውን ህዝብ አንጉቶ፤ ለድርድር የቀረቡትን የበለጠ አዋግቶ መሸሽ ስለሆነ፤ ቤተ ክርስቲያንን በደሏት ብለን ከምንወቅሳቸው ሰዎች የከፋ በደል ነው። ሊቃውንት አባቶች እናንተ በገባችሁበት ፈታኝ ሁኔታ ላይ ገብቶ አሸንፎ ለወጣው ጽኑዕ የቤተ ክርስቲያን ሰው መታሰቢያ ይሆንለት ዘንድ የተደረሰለትን ቅኔ ትምህርት እና አቅጣጫ የሚያሳይ ቅርስ ነውና ላስታውሳችሁ።

"ክቡድ ቀርን ኤዎስጣቴዎስ፤ ዘበቶልክ ለነ በዘመነ ወንጌል ሐዲስ፤
እስመ ልበ አድባር ከደነ፡ ኃይለ ሃይማኖትከ ጢስ።
አመ ዕድወትከ ቀላየ በየብስ።
አምቅቡአነ ዘይት መንፈስ ቅዱስ፤ ዘይትባየጸከ መኑ በፍኖተ ሞገድ ግብረ ነፋስ።
እመኒ ተባየጽከ በዕድወተ ዓባይ ተርሴስ፤
በበትር ወሐሜላት፤ ሙሴ ወኤልያስ፤
በመንግስተ ሰማይ ዛህን በገነተ ሄኖክ መርስ፤
አልቦ ዘየዓብዮ ለአጽፍከ ዮሐንስ"

ይህ ቅኔ ከገባችሁ ማንም ሳይጠይቃችሁ የናት ቤተ ክርስቲያናችሁ ሁኔታ አስገድዷችሁ በፈቃዳችሁ መንቀሳቀስ የጀመራችሁትን ቀርቶ ሙታንን ከመቃብር የሚቀሰቅስ ነው።

"ብዙወች ነበሩ አገር ያፈራቸው፤
ዳሩ ምን ይሆናል ሞት ነው ያጠቃቸው" የሚለው ቅኔ በድምጻዊቷ ጉሮሮ በኩል ለመላ ኢትዮጵያውያን እንዲደርስ ያደረጉት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ናቸው።

"ክረምት ባይመጣ ሁሉ ቤት።
እንግዳ ባይመጣ ሁሉ ሴት" የሚባለው ባህላዊ አባባልም አለን። በሰላም ጊዜ ሁሉ አዋቂ፡ ሁሉ ጀግና ነው። አፋችንን የፈታንበት፤ ዛሬም የምንደግመው ዳዊት "ኩሉ ጻድቅ በጊዜ ርቱዕ" የሚለው ከባህላዊው አባባላችን ጋራ የሚስማማ ነው። ባህላውያን አባባሎቻችንም ሆኑ የሊቃውንት አባቶቻችን ቅኔዎች የመነጩት የቅኔ መጻሕፍት ከሚባሉት ቅዱሳት መጻሕት ነው።

አገር በሽብርተኞች ስትናወጽ ዜጋ የሆነ ሁሉ ራሱን ለመከላከልም ሆነ አገርን ለማረጋጋት በሚደረገው ፍልሚያ ለመሳተፍ በደህና ጊዜ ያስቀመጠውን መሳሪያ ከያለበት እየፈለገ እንደሚወለውል፤ እኛም የእምነት የሞራልና የቁርጥ ታማኝነት ምንጮች የሆኑት ሊቃውንት አባቶቻችን ያስቀመጡልን ቅኔዎች ራሳችንን የምንመዝንባቸው አካባቢያችንንም የምንፈትሽባቸው ናቸውና በዚህ ጊዜ ልንዳስሳቸው ይገባል።

የአባቶቻችን ቅኔዎች መሠረታቸው የቅኔ መጻሕፍት ተብለው የሚጠሩት ቅዱሳት መጻሕት ናቸው ብያለሁና፥ ጥቂቶችን ከጥቂት መጻሕፍቶች ልጥቀስ።

"በሊዓ ብዙህ መዓር አኮ ሠናይ ወየሀምግ ከርስ፡ ወየኃይል ለረቅይ" (ምሳ ፳፭፡ ፳፯) ይህም ማለት "የሚጣፍጥ ማር አብዝቶ መብላት ጥሩ አይደለም። ሆድ ይነፋል። በመጨረሻም ያስታውካል" አንገትን እያቀለሰለሱ ያለቦታውና ያለተገቢው ትህትና በመስጠት ባለስልጣንን መቅረብ ረብ የሌለው ጥቅም ፍለጋ ነው። በዚህ መንገድ የሚገኘው ሹመትና ሽልማት ያውርዳል። ከመካከላችሁ ይህ መሳይ ባህርይ ያለው ሰው ካለ ቀልምሞ በመውሰድ ይዟችሁ ገደል እንዳይገባ ተጠንቀቁ!

የሰላም ልኡክ ብላችሁ በፈጠራችሁት ድርጅታችሁ በጨለመበት ጊዜ ብቅ በማለታችሁ ዘላቂ ቁም ነገር ትሰራላችሁ በማለት ከነ ስብሀት ነጋ በቀር ሁሉም ደስ ብሎት ተቀብሏችኋል። ሁሉም አሁን በገባበት አረንቋ ሲዘፈቅ ድምጻችሁ በመጥፋቱ፤ ከናንተ ጋራ የቆመው ህዝብ "መኑ የአምር ከመ ትጠፋዕ በከዊነ ተነ ጊሜ" (መቃ ፱:፱-፲) ማለትም፦ ፍለጋው እንደማይገኝ እንደ ጉም ሽንት ተኖ ጠፍቶ እንደሆነስ ምን እናውቃለን? እየተባባለ ነው።

ሽባና ተልካሻ ከሆነ ከዘር ከጎሳና ከክፍለ ሀገር ከጥቅማ ጥቅም በሽታ ተላቃችሁ፣ ራሳችሁን ካሉባልታ አግልላችሁ "ብእሲሰ ጠቢብ ያፈቅር ሰሚአ መጻሕፍት። ወዘሰ ይናፍቅ ወኢይትአመን በመጽሐፍ ይከውን ከመ ሐመር እንተ ታንኮልል መአከለ ዐውሎ" (ሲራ. ፴፺፣ ፪) የሚለውን ምክር ተከተሉ። ማለትም፦ አዋቂ ሰው ከመጻህፍት በሚያገኘው ጥበብ ይመራል። አላዋቂ ሰነፍ ሰው ግን ባሉባልታ ይደናበራል። በራሱ ጸንቶ መቆም ያቅተዋል። በነፋስ እንደሚናወጽ መርከብ ይዋዥቃል" በሚለው በጥበበኛው ሲራክ ሚዛን ራሳችሁን መዝኑ!

"ብእሲ ምሁር ዘተገሰጸ ብዙሀ የአምር ወዘአፈድፈደ ጥበበ ይነግር" (ሲራ ፴፬:፱) የሚለውን በመመልከት ብቻችሁን እንወጣወለን ብላችሁ አትሞክሩ። ከናንተ ይልቅ በልምድ በአመክሮ የበሰሉትን ሊቃውንት አሰባስቡ!

የምትከተሉት የቀኖና፥ የሞራል፥ የህግና የነገረ መለኮት ጉዳይ ስለሆነ "ሁለት ልብ ሆናችሁ ወደ ህግ አትቅረቡ (ሄኖክ ፴፬፣ ፱) የሚለውን ምክር አትርሱ። ሁሉም አሁን በገባበት አረንቋ ሲዘፈቅ ድምጻችሁ በመጥፋቱ፤ ከናንተ ጋራ የቆመው ህዝብ "መኑ የአምር ከመ ትጠፋዕ በከዊነ ተነ ጊሜ" (መቃ ፱:፱-፲) ማለትም፦ ፍለጋው እንደማይገኝ እንደ ጉም ሽንት ተኖ ጠፍቶ እንደሆነስ ምን እናውቃለን? እየተባባለ መሆኑን እያሳሰብኳችሁ እሰናበታችኋለሁ። ይህን በመሰለ ፈታኝ ዘመን ላይ ቤተ ክርስቲያን ስትወድቅ፥ ህዝበ ክርስቲያኑ ሀላፊነቱን እንዴት እንደሚወጣ በመመሪያች ተጽፎ የተቀመጠውን በሚቀጥለው ጦማር አቀርባለሁ።

**ይቆየን::**

***ለሌሎች ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለውን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ::***

http://www.medhanialemeotcks.org/